# ኢትዮጵያዊነት

## ክፍል ፩

*ከቀመሩ ደሳለኝ*

ኢትዮጵያዊነት የኢትዮጵያን ክብር፣ ልዕለ- ታላቅነት በከባድ አደራ ያባቶቻችን ጽንሰ ሃሳብ የወረሰንበትን፣ እንድናስታውስ የሚያሳስበንና እንድንተገብር የሚያበረታታን አገራዊ ፍቅርና የነፃነት ቅርስ ታሪክ ነው። ይህ ቅርስ ሁላችንንም በአንክሮ አርቀን እንድናስብ፣ ለአገራችንና ለመጪው ትውልድ ያለንን ምኞትና ሕልም እውን ለማድረግ ተግተን መስራትን ነው።

ኢትዮጵያዊነት ክቡር የሆነ ለአገር ሥነ-ምግባር መልካምነት መግለጫ ነው። ኢትዮጵያዊነት የሚተላለፍ ከትውልድ ትውልድ የሚሸጋገር፣ የማያረጅ ጊዜ የማይሽረው፣ የማይሰረዝና የማይደለዝ፣ የማይሞት የየትውልዱ አገራዊ ምግባርና ፍቅር ነው።

ኢትዮጵያዊነት ከኢትዮጵያዊ- ከዜግነትም የላቀ፣ የጠለቀ ምስጢርነት ያለው የወገን ፍቅር ስሜት መግለጫ ኃይል ነው። በአገር ጉዳይ ተቆርቆሪ፣ አገር ከሁሉ በፊትና መጀመሪያ የሚል ራሱን ለአገር ወገን አስቀድሞ የሚሰጥ የኅብረተሰብ ጠባቂ ነው።

ኢትዮጵያዊነት፣ የሕዝብ ደህንነት፣ የአገር ሰላም ብልጽግና፣ መብትና እኩልነት አስከባሪ ዘብ አዳሪ ነው። አገር ወገን ሲበደሉ ታጥቆ የሚነሳ የአንዱ ችግር የሁሉም፣ የብዙውም የእያንዳንዱ እንደሆነ ተገንዝቦ ኃላፊነት የሚወስድ፣ <u>ኢትዮጵያ እኔ ነኝ</u> የሚልና የኢትዮጵያን ጉዳይ ተግባራዊ የሚያደርግ ኃላፊነት ነው።

ኢትዮጵያዊነት አገር ሲበደል አሻፈረኝ ባይ እንጂ፣ ወንድም/እህት፣ ወዳጅ፣ ጐረቤት ሲጨቆን፣ ግፍ ሲደርስበት በእኔ ካልደረሰ ብሎ በቸልተኝነት አይመለከትም።

ኢትዮጵያዊነት ፊጥኖ ደራሽ የጋራ ኅብረተሰብ አገልግሎት ሰጭነት <u>አገር ማዳን</u> ነው።

ኢትዮጵያዊነት ዓላማና ግብ ያኖራቸውን ኢትዮጵያንና ሕዝቧን በአንድነት አጠንክሮና አበልጽጎ በእኩልነት መጠበቅና ለመጪው ትውልድ በኩራት ማውረስ ነው እንጂ፣ እንደ ወያኔ በጎጠኝነት፣ በውሸትና በክህደት ሺ-ዓመታት በአንድነት የኖሩትን፣ በእምነት የበለጸጉትን፣ ማጣላት፣ ማናከሰና ማበጣበጥ፣ ማጋጨትና ማለያየት፣ ለራስ ጥቅም ማዋል አይደለም። ይህን መቃወምና ከኢትዮጵያ መሬት ላይ ማስወገድ የኢትዮጵያዊነት ተቀዳሚ ተግባር ነው።

ኢትዮጵያዊነት ትከሻ ለትከሻ፣ ተጠባብቆ፣ ክንድ ለክንድ አስተባብሮ አገርና ወገንን መጠበቅና ማስከበር ሲሆን፣ ለዚህም ደግሞ ወዳጅና ጠላቱን በሚገባ ለይቶ፣ አንጓሎና አበጥሮ፣ አቻውን አውቆና ተረድቶ፣ ከማንና ለምንስ ጉዳይ መነጋገርና መደራደር እንዳለበትና ግልጽ ግብን የሚያስቀምጥና ለተግባራዊነቱም ቁርጥ አሰላለፍንና አደረጃጀትን የሚያሳይና የሚያረጋግጥ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ የሚሰማማ እድገትንና ብልጽግናን፣ ኅብረተሰባዊ ጥንካሬን የሚያፋጥንና ዲሞክራሲያዊ- ሰብዓዊ መብቶችን እውን የሚያደርግ ሥርዓትን- መፍጠር ነው።

ኢትዮጵያዊነት የፈረንጅ ትምህርት ተምሮ ፈረንጅ ለመሆን መሞከር፣ ጥራዝ ነጠቅነት ሳይሆን ጥበብን ቀስሞ ራስን መሆን፣ በራስ ባሕልና ማንነት መኩራትና በእራስ እኔነት መገኘት ነው።

በክህደት ላይ የተመሰረተ አጉል ፈረንጅነት እኔነትን መካድ የትም አያደርስም። ወያኔ የሚያስተምረው ክህደትና ውሸት፣ የዘራፊ የከፍለህ ግዛው የፋሽስትና ፀረ-ኅብረተሰብ ባህሪ ነው።

ኢትዮጵያዊነት በቀደምት አባቶች/እናቶች ታሪክ የሚኰራ ነው። ብሔራዊ አሀዳዊ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነቷን አስከብሮና ጠብቆ ያወረሱን ኢትዮጵያዊ ጀግኖች የዜግነት የውዴታ- ግዴታ ቃል-ኪዳን እምነት ውጤት ነው። ሁሉንም የተለያዩ ቋንቋና ባህል ኅብረተሰብ በእኩልነት በአንድ ኅብረተሰባዊ መከባበርና መወራረስ አያይዞና አጣምሮ በባህሉ በወግና ፈሊጡ የማንነት ውጤት አዋህዶና የራስ አድርጐ ያኖረን ኢትዮጵያዊነት ነው።

ለምሳሌ አፄ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ለኅብረተሰባዊ እኩልነት መብት መጠበቅ ያደረጉት ጥረት ለዚህ የሚጠቀስ ነው።

> "የአሳባችን ዋና ዓላማ የንጉሰ-ነግሥት መንግሥታችን ተወላጅ ዜጎቻችን ሁሉ በመጠናቸው በምክር ቤት ውስጥ በሚገባ እንደራሴ እንዲኖራቸውና በዘርም ሆነ በሃይማኖት በመካከላቸው አንድም ልዩነት እንዳይኖር ለማድረግ ነው። ማናቸውም ኢትዮጵያዊ ትክክል መብት እንዲኖረውና የተወደደው ሕዝባችን ሁሉ የአንድ ትልቅ ቤተሰብ ተወላጆች ሆነው በወንድማማችነት እኩል እንዲኖሩ ዘወትር የተከተልነው ዓላማ ነው። በንጉሠ-መንግሥቱ ግዛት የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ የሃይማኖታቸውን ሥርዓት አክብረው በነፃነት ለመፈጸም አይከለከሉም።"

ይህ ኢትዮጵያዊ እኩልነትን የሚያንጸባርቅ የሁላችን መኩሪያ የአስተዳደር መሪ ቃል ነው። ይህን መካድ ወንጀል፣ የራስን ማንነት ማጥፋት የክህደት በሽታ ነው። ወያኔ በቋንቋ ጎጠኝነት ኅብረተሰባችንን ለመከፋፈል የሞከረው በክህደት ላይ ተመስርቶ ነው። ወያኔ በቋንቋ ልዩነት ያጫቀየውን የፖለቲካ መንገድ ተከትሎ መሄድ ለአደጋ መጋለጥ ነው። የሰው ልጅ አንድ የሰው ዘር ብቻ ነው። <u>ቋንቋ የዘር መለያ አይደለም</u>። ተምረው የሚያገኙት የተፈጥሮ ጥበብ ነው። የተለያየ ዘር የምናውቀው የእህል ዘር ብቻ ነው (ገብስ፣ ስንዴ፣ ባቄላ፣ ሽንብራ ወይንም ጓያ አይደለም) ሰው ሰው ነው። ሰው በሰውነቱ ክቡር ነው።

ኢትዮጵያዊነት ጭቆና ሲበዛ አሻፈረኝ ብሎ ከወገን ጎን የሚቆም፣ ችግርን የሚጋፈጥ፣ ደጀን የሚሆን፣ አንገቱን የማይደፋ፣ የማያፈገፍግ፣ የማይሸሽ፣ የማያሳጣ፣ ደፋርና ጀግና ጀብዱ የሚሰራ፣ ነፃነትና ሰላም እምነቱ ያደረገ፣ ፍፁም ተስፋ የሚጣልበትና መስዋዕትነትን የሚከፍል ተዋጊ ጦረኛ፣ ሰማዕታት መሆን የሚችል ጠባቂ ኃይል ነው።

ኢትዮጵያ የሰው ዘር ለመጀመሪያ ጊዜ ከተቀመጠበት ብድግ ብሎ በሁለት እግሩ የቆመባት ምድር ናት። የሚኰራባት አገር ናት። ኢትዮጵያዊነት አሃዳዊነት ነው።

ኢትዮጵያዊነት የተማረውን፣ ያደረጉትን መሆን ሳይሆን ጥበብን ቀስሞ ራስን መሆን ነው። ኢትዮጵያዊነት ራስን አውቆ በራስ መኩራትና አገርን ማስከበር ነው። ኢትዮጵያዊነት የኢትዮጵያ ብቻ የሆኑ፣ የስሜት መገለጫዎች የነበሩዋትን የሚጠብቅ ነው።

ኢትዮጵያዊነት የኢትዮጵያ የሆነውን ሁሉ በጸጋ ስር መሰረቱን፣ ማንነቱን ተምሮና አውቆ በባህል፣ በወግና በኑሮ ሥርዓቱን የራሱን ተምሮ፣ መርምሮ የሚሻሻለውን አሻሽሎ እያደሰና እያሰመረ ከባእድ ጥገኝነት ርቆ የዚያ ባለቤት በመሆኑ የሚኰራ፣ የሚመካ፣ ራሱ ተከብሮ አገርን የሚያስከብር ትውልድ አስተምሮና አንጾ ማውጣት ነው።

ኢትዮጵያዊያንን ከአገራቸው ጋር አቆራኝቶ የሚያኖራቸው የአገር ትዝታና ናፍቆት አላቸው። ኢትዮጵያዊነት በመልካቸው ብቻ ሳይሆን በመንፈሳቸው፣ በስሜታቸው፣ በምኞታቸው፣ በጠባያቸው፣ ባስተሳሰባቸው፣ በስራቸው ከሌሎች ሁሉ ለይቶ ኢትዮጵያዊያን አሰኝቶ የሚያኖራቸው ይህ ምግባር ነው።

ኢትዮጵያዊነት ቅርስ፣ ሃብት ተወራራሽ፣ በጀግንነት አገር ማስከበር ነው። ኢትዮጵያዊነት ሕያው፣ አልፋና ኦሜጋ ምንጊዜም የማያልፍ፣ ምንጊዜም የማይሞት፣ የማይለወጥ አገራዊ ክብር ነው።

***ኢትዮጵያዊነት አህዳዊ ኢትዮጵያ የታነፀ፣ የማይደፈር፣ የማይገሰስ፣ የማይደፈርስ የጠራ አገር ወይንም ሞት ብሎ ለኢትዮጵያና ለሕዝቦቿ አንድነትና እኩልነት የሚሟገት ኃይልና ጠበቃ ነው።***

***ምንጊዜም ኢትዮጵያ !***

***ኢትዮጵያዊነት ቃል ኪዳን ነው !***

***ኢትዮጵያዊነት ያሸንፋል !***